**ማንነት** ታጠቅ መንጂ: 17 February 2016

ክፍል 1

በእኔ እይታ አሁን ያለንበትን ዓለም ሁለ-እንተናዊ እድገት፤ የማንነት ማስመስከርያ ውድድሮች ውጤት ነው እላለሁ ። ብሄር/ብሄረሰቦች፣አገሮች፣ አሁጉሮች ፣ግለሰዎች ፣ቡድኖች ወዘተርፈ ለማንነት ይወዳደራሉ ።

- ማንነት - በመልካም አስተዳደር ፤አገርንና ዜጎችን በዲሞክራሲያዊ መተክሎች (principles) በማስተዳደር ናሙና የመሆን ማንነት
- ማንነት- በጥንታዊ ሥልጣኔ ፤በጥንታዊ ቅርጻ ቅርጽ በመታወቅ
- ማንነት - በዘመናዊ ኢንዱስትሪ ፣ቴክኖሎጂ ፣ኮሚኒኬሽን ወዘተርፈ ሥልጣኔ በመብለጥ/በመቅደም
- ማንነት - በንጥረ ነገሮች (በኬሚስትሪ) ፣ በሃይል ምንጭ (በፊዚክስ)፣ በመደሃኒት ቅመማ ወዘተ.. ጥናትና ምርምር ለኖብል ሽልማት በመብቃት
- ማንነት - በጠፈር ሳይንስ ምርምር ቀድሞ በመገኘት፤ የበላይነት በማረጋገጥ
- ማንነት - በሥነጽሁፍ ፣ በፍልስፍና ፣በማህበራዊ ሳይንስ ፣በኤኮኖሚክስ ሳይንስ ጥናቶች እውቅና በማግኘት
- ማንነት - ዓለምን በማራጋጋትና ሰላም በማስፈን ሥራ - ለኖብል ሽልማት በመብቃት
- ማንነት - በዘመናዊ ወታደራዊ ችሎታ፣ ብቃት፣ እስትራተጂ፣ ስልት፣ የጦር መሳርያ የበላይነት በመያዝ
- ማንነት - በኦለምፒክ በተለያዩ የስፖርት ግጥሚያዎች - የወርቅ ፣ የብርና የነሃስ መዳሊያ በማግኘት
- ማንነት-በጦር ሜዳ ጠላትን አሸንፎ ብሄራዊ ሉዓላዊነትና የሃገርን ጥቅም የማስከበር ማንነት፤
- ማንነት - ከባዕዳን አገዛዝ ነጻ ሆኖ የመኖር፣ ብሄራዊ ሉዓላዊነትን፣ታሪክን፣ ባህልን፣ ቋንቋን፣ እኔነትን ወዘተ..ሳያስደፍሩና

ሳያስነኩ በኩራት የመኖር ማንነት። እነዚህን ማንነቶች በቅኝ ገዢዮች ሥር ከወደቁ -የሚኖረው ግንኙነት - የባሬያና የጌታ ግንኙነት ነው የሚሆነው

እናንተ ግማሽ ሰው ናችሁ ፣እናንተ ከእኛ በታች ናችሁ ፣እናንተ እኛን ማገልገል አለባችሁ ፣የተፈጥራችሁት በእኛ እንድትገዙ ነው - በማለት በንቀትና በትምክህት ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ የገሰገሰውን የጣሊያን ሠራዊት የካቲት 23 ቀን 1888 አደዋ ላይ በጀግኖች አያቶቻችን ድባቅ ተመታ ። ስለሆነም የማንነቶች ሁሉ ማንነት አጎናጽፈውናል

ለእኛ ብቻ ሳይሆን ነጭን በጥቁር ሰው እንደሚሸነፍ ለሞላው ዓለም ጥቁሮች አስተምረው አልፈዋል ።

“በአደዋ ጦርነት የምኒሊክ ሠራዊት 40%ን የኢጣሊያን ወታደር ገድለዋል ፤ አቆሰለዋል ። ከጦርነቱ በኋላ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ሉዕካን ወደ አዲስ አበባ ሄደው አጼ ምኒሊክ በአፍሪካም በአውሮፓም ከወቅቱ ሃያል መንግሥታት አንዱ መሆናቸውን እውቅና ሰጥቷቸው ተመለሱ” በማለት (ሪቻርድ ፓንክረስ) መሰከሯል።

“ኢትዮጵያውያን አርበኞች የማረኩዋቸውን 1800 ኢጣሊያኖች- ስብዕና በተካሃነ ሁኔታ ተስተናግደው -ሁሉንም በሰላም ወደ አገራቸው ተመልሰዋል ፤ ያንን በጎ ሥራ - በምኒሊክና በአውሮፓውያን መካከል መልካም የዲፕሎማሲ ግንኙነት እንዲፈጠር ረቷል” በማለት (አሼዲዝ ቴራዚያን) መስክሯል ።

እ.አ.አ ከ 1888 -1940 የኖረው -የራስተፈሪያን እምነት መሰረት የጣለውና የሞላ ዓለም ጥቁሮች መሻሻል ድረጅት (ዩኒቨርሳል ኔግሮ ኢምፕሩቭሜንት አሶሴሽን) መሪ የነበረው ጃሜካዊው ማርከስ ጋርቪ - ከአደዋ ጦርነት በኋላ ፡-

-ሁሉንም ጥቁሮች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት እንዲኮሩ

-ኢትዮጵያ ሁሉንም ጥቁር ነጻ ታወጣለች

-እኛ ጥቁሮች ተሰቃይተናል፣ ወድ ኢትዮጵያ መሄድ አለብን (ባክ ቱ ኢትዮጵያ) ወዘተ.. እያለ ይሰብክና ያስተምር ነበር ።

ነገርግን በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ወቅት ሃይለሥላሴ ሸሽተው ወደ አውሮፓ ሄደዋል የሚል ወሬ በመስማቱ -በሃይለሥላሴ እና በኢትዮጵያ ላይ የነበረው ተስፋና ኩራት ወደ አሉታነት ተለወጠ ። ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ በብስጭትና በህመም ምክንያት በለንድን ከተማ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ

ክፍል 2

## አደዋ

ማንነታችን የተመሰከርብሽ

ያያቶቻችንን ጅግንነት ያስመሰከርንብሽ

የጥቁር ሕዝብ የነጻነት ጮራ የፈነጠቀብሽ

የጥቁር ሕዝብ የድል እምቢልታ የተነፋብሽ

እምቢ አሻፈርኝ በባዕድ አልገዛም ያልሽ

ከአጥናፍ እስከ-አጥናፍ የታወቅሽ

ሁሉንም የታርክ ማህደር የመዘገበሽ

ጣሊያን ባንቺ ተረማምዶ ኢትዮጵያዊ/ዊት ባሬያ የማግኘት ምኞትን ያከሸፍሽ

አንተቿን ረጋግጦ ኢትዮጵያን ቅኝ የማድረግ ምኞትን ከንቱ ያደረግሽ

አንቺን አዋርዶ ኢትዮጵያን ለማዋረድ ያሰበሽን ያምበረከክሽ

አንቺን ቀብሮ ኢትዮጵያን ለመቅበር የከጀለሽን ቀድመሽ የቀበርሽ

በክፉ ለተመኙሽ የማትመቺው አደዋ

ሰማይሽ ፀረ ጠላት

አየርሽ ፀረ ጠላት

ወንዞችሽ ፀረ ጠላት

አዘእርቶችሽ ፀረ ጠላት

ተራሮችሽ ፀረ ጠላት የነበሩ አደዋ

ሁሌ የምንወድሽ አደዋ

ሁሌ የምንጠራሽ አደዋ

ሁሌ የምናሞግስሽ አደዋ

በየዓመቱ የምንዘክርሽ አደዋ

ባለውታዋ አደዋ

ገዳሟ አደዋ

አድባራሟ አደዋ

መንፈሰ ቀናዋ አደዋ

መኩሬያችንና መመኪያችን የነበርሹ አደዋ!

ዛሬ ምንካሽ አደዋ?

ምነው አጥፊዮችሽን ጽንሰሽ ወለድሽ?

ምነው ባንዳዎችን ኮትኩተሽ?

መለስ ለገሰ ዓይነቱ የባዕድ ቅጥረኞች

ካሃዲዎች፤ታሪክሽን ፤ተረተረት ነው ባዮች

ሰደቅ ዓላማሽን የሚረግጡ፤ጨርቅነው ባዮች

'አደዋ' በትግሬ ላልተወለዱ ኢትዮጵውያን ምናቸውም አይደለም ባዮች

ዳር ድንበርሽን ቆራርጠው ለባዕድ የሚሸጡ ወንበዴዎች

ወገን በወገን ላይ የሚያስነሱ፤ የሚያሸፍጡ መሠሪዎች

ዛሬ ምነካሽ አደዋ!

ምነው ስምሽን በከልሽ!

ምን በከለው ማህጸንሽ!

ምን መረዘው አብራክሽ!

የያኔ ጠላቶችሽ ደም በማህጸንሽ ስለቀበርሽ ይሆን?

የያኔ ጠላቶሽ አጥንት በከርስሽ በመያዝሽ ይሆን?

እነመለስ ዜናዊ እናቶች በዚያ ላይ የበቀለ እህል በልተው ይሆን?

በዚያ ላይ የሚወርድ ወንዝ/ምንጭ ውሃ ጠጥተው ይሆን?

ምን አስቀየምንሽ አደዋ?

ምን በደልንሽ አደዋ?

ምን አስከፋንሽ አደዋ?

በድለንሽ እንድሆን ይቅር እንድቲይን እንማፀንሽ

---------------- ማሪን! ማሪን! እንልሻለን

በድለሽንም እንደሆን ይቅር እንድ እንልሽ ተማፀኝን

------------------እንድንምርሽ ተማፀኝን

በጋራ ብሄራዊ ስሜት፣ስነልቦናና ትግል ወያኔ እናምበረከካልን!

ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ አልፋና ኦሜጋ ናችው !